# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 192 ጥር ፲ 2004 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

**ወጣት መምህር የኔሰው ገብሬ**

*“በደል በዛ!!! ፍትህ በሌለበት አገር መኖር አልችም!!! በዚህ ሁኔታ መኖር ኑሮ አይባልም!!! ግፍና መከራ እያየሁ መኖር አልችልም!!!”*

እያለ ቤንዚን በራሱ ላይ አርከፍክፎ እሳት ለኮሰ። ኅዳር 4 ቀን 2004 ዓ.ም. ኢትዮጵያም አንድ በፍትህ እጦት የተከፋና የተቆጣ ልጇን አጣች። ለእኛ ግን ትምህርት ሆነ። የየኔሰው ገብሬ ቁጣ በውስጡ የነበረው ፍርሃትን አሸነፈ።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በሽብርተኝነት ወሂኒ ያወረዳቸው ጋዜጠኞችና ተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እንደተጠበቀው ጥፋተኞች ናቸው የሚል ብይን በወያኔ ፍርድ ቤት ተላለፈባቸው

በሰሜን አፍሪካና መካከለኛው ምሥራቅ በአምባገነን መሪዎች ላይ የደረሰው የህዝብ ቁጣ የፈጠረበት ድንጋጤና ስጋት ያስጨነቀው ዘረኛው መለስ ዜናዊ በሽብርተኝነት የፈጠራ ክስ እስር ቤት እያማቀቃቸው በሚገኘው ጋዜጠኞችና የፍትህ ታጋዮች ላይ እንዲወሰን ያስተላለፈው ቅጣት ህጋዊ ሽፋን ለማስጠት የተጀመረው ድራማ ወደመገባደዱ እንደተቃረበ የግንቦት7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከው ዘገባ አስታወቀ።

የድራማው መጀመሪያ ክፍል በሆነው የፈጠራ ክስ ከአገር ውጪ በሚኖረው ጋዜጠኛ ኤልያስ ክፍሌ መዝገብ የተከሰሱት ፖለቲከኞች እና ጋዜጠኞች ላይ በእንዳሻው አዳነ የተመራው የወያኔ ፈደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዛሬው ቀን ባስተላለፈው ውሳኔ ጋዘጠኛ ኤልያስ ክፍሌ በ4 የሽብርተኝነት ክሶች ጥፋተኛ ተብሎአል።

ከመለስ ዜናዊ በቀጥታ የሚተላለፈው የቅጣት ውሳኔ በሆድ አደሩ ሽመልስ ከማል በኩል በተዋረድ የሚደርሳቸው የፈደራል ፍርድ ቤት ዳኞች ተብዬዎች የፍርድ ሂደቱን ህጋዊ ለማስመለስ በቀጠሮ ጋጋታ ተወንጃዮቹን ላይና ታች ሲያመላልሱ ከሰነበቱ ቦኋላ በዛሬው ዕለት ባስተላለፉት የጥፋተኝነት ውሳኔ የኢትዮጵያ አንድነት ሊቀመንበር የሆኑት አቶ ዘሪሁን ገብረእግዚአብሄር፣ የአውራምባ ታይምስ ምክትል ዋና አዘጋጅ የነበረውን ጋዜጠኛ ውብሸት ታየ፣ የፍትህ ጋዜጠኛ አምደኛ የሆነችውን ርእዮት አለሙን እና ሂሩት ክፍሌን በሶስት ክሶች ጥፋተኛ ናቸው ብሎአቸዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የጋምቤላ ክልል ፕሬዳንት ሰሞኑን የሰጠው ምስክርነት በ1996 ዓም አኝዋኮች ላይ የተፈጸመውን ጭፍጨፋ ህግ ፊት ለማቅረብ የሚደረገውን ጥረት ያግዛል ተባለ

በመለስ ዜናዊና በወቅቱ የፈደራል ጉዳዮች ሃላፊ በነበረው አቦይ ጸሃዬ ትዕዛዝ በጋምቤላ የአኝዋክ ብሄረሰብ አባላት ላይ እንደፈረንጆች ዘመን አቆጣጠር ዲሰምበር 2003 የተፈጸመው ጭፍጨፋ አንድን ዘር ከምድረገጽ የማጥፋት ወንጀል አካል ነውና ጉዳዩ በገለልተኛ ወገን ተጣርቶ ተጠያቂዎቹ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት ይቅረቡ ሲል ሲወተውት የቆየው የሂውማን ራይትስ ዎች ተመራማሪ፤ ሰሞኑን በጋምቤላ ክልል በተካሄደው ግምገማ የክልሉ ፕሬዝዳንት ኦማት ኦባንግ የሰጠዉ ቃል የወያኔ ወታደሮች ፈጽመዋል የተባለውን የጭፍጨፋ ጉዳዩ እንደገና እንዲቀሰቀስና እንዲታይ ማስቻል ይኖርበታል ማለታቸውን ቪ ኦ ኤ የአማሪኛው ዝግጅት ከትናንት በስቲያ ማክሰኞ ስርጭቱ ዘገበ።

ታዋቂው የሰብአዊ መብቶች አቀንቃኝ ድርጅት "ሞትን እዚህ እየጠበቅን ነው፤ በኢትዮጵያ የጋምቤላ ክልል ሰዎች በሀይል ከቦታቸው እየተፈናቀሉ በመስፈር ላይ ናቸው" በሚል ርእስ ባወጣው መግለጫ የመለስ አገዛዝ ሰፈራ በሚለው መርሀግብሩ ከ70 ሺ በላይ የጋምቤላ ተወላጆችን ከቀያቸው አፈናቅሎ፣ ምግብ፣ የእርሻ መሬት፣ የጤና እና የትምህርት አገልግሎት በሌለበት ቦታ አስፍሯቸዋል ሲል መክሰሱን ምክንያት አድርጎ ቮ ኦ ኤ ያነጋገራቸው የድርጅቱ ተመራማሪ ቤን ራዎልስ ለሠፈራ በግዴታ ከቀያቸው ከተፈናቀሉ ቦኋላ ለከፍተኛ ኑሮ ችግር በመዳረጋቸው ህይወታቸው የተቀጠፈ ሰዎች ቀብር ሥነሥረዓት ላይ መገኘታቸውን አረጋግጠዋል።

በሰፈራው አንሳተፍም ባሉት ሰዎች ላይ የሀይል እርምጃ እንደተወሰደባቸዉም በሪፖርቱ የገለጸው ሂውማን ራይትስ ዎች፤ ሰፋሪዎች በግዳጅ ከቦታቸው እንዲፈናቀሉ በመደረጉ ባለፈው አንድ አመት ውስጥ በርካታ ህይወት መጥፋቱን የምግብ አቅርቦትም ባካባቢዉ ተሟጦ ማለቁንና እንዲሁም የጸጥታ ሀይሎች ተደጋጋሚ የሀይል ጥቃት በማህበረሰቡ ላይ መሰንዘራቸዉንም ጠቅሷል።

የሂውማን ራይትስ ወች የአውሮፓ ተወካይ የሆኑት ጃን ኢግላንድ ከኢሳት ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ ሂውማን ራይትስ ወች መረጃውን ያጠናከረው በክልሉ ከሚገኙ ሰዎች ጋር በመነጋገር መሆኑን ገልጠው፣ አሁን የተጀመረው ሰዎችን በሀይል ከቦታ የማፈናቀል ጉዳይ ሁኔታዎች ምቹ እስከሚሆኑ ድረስ በአስቸኳይ እንዲቋረጥም ጠይቀዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## በአፋር ብሄራዊ ክልል በተገደሉት 5 የውጪ አገር ዜጎች ግዲያ ውስጥ የወያኔ እጅ ሊኖርበት እንደሚችል ተገለጸ። የአፋር ህዝብ ፓርቲ ግዲያውን አውግዞአል

ከትናንት በስቲያ ማክሰኞ ጥር 7 ቀን 2004ዓ/ም በቆላማው የአፋር ክልል ጉብኝት ላይ እንዳሉ ተገድለዋል የተባሉት 5ቱ የውጪ አገር ቱሪስቶች ግዲያ ጉዳይ ላይ የወያኔ እጅ ሊኖርበት እንደሚችል ፍጹም እንደማያጠራጥር ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ በመስተዳደሩ ውስጥ የአንድ ሥራ ዘርፍ ሃላፊ የሆኑ ሰው ለዘጋቢያችን ገለጸዋል።

እንደኚህ ሰው መረጃ ቱሪስቶቹ በተገደሉበት አካባቢ በወያኔ የሚታገዘው የቀይ ባህር አፋሮች ዲሞክርሲያዊ ድርጅት በአካባቢው በሰፈረው የወያኔ ጦር ሙሉ የመሳሪያና የሰው ሃይል ድጋፍ እየተደርገለት ይንቀሳቀሳል። ይህ በሆነበት ምድር አካባቢውን በሚገባ ጠንቅቆ በሚያውቁ አስጎብኙዎች የሚመራ ቱሪስቶች ቡድን ላይ ቀርቶ ወፍ ላይ ተኩሶ ማምለጥ አይቻልም።

በግዳጅ ሰፈራ ምክንያት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከአካባቢው ህዝብ ጋር ሆድና ጀርባ እየሆነ የመጣው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ እየተባባሰ የመጣውን የህዝብ ተቃውሞ በጸጥታ ጥበቃ ሥም ለመደፍጠጥ እንዲያስችለው እንዲህ አይነት ወነጀል ከማቀነባበር ወደኋላ እንደማይል ያላቸውን እርግጠኝነት አክለው ገልጸዋል።

ይህ በዚህ እንዳለ የአፋር ህዝብ ፓርቲ ግድያውን በጽኑ እንደሚያወግዝ መግለጹን የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ኢሳት በትናንትናው የዜና እወጃው ዘገበ።

የፓርቲው የውጭ ግንኙነት ሀላፊ የሆኑት ዶ/ር ኮንቴ ሙሳ ለኢሳት እንደተናገሩት በውጭ አገር ዜጎች ላይ የተወሰደውን እርምጃ ፓርቲያቸው ያወግዘዋል። ድርጊቱን የወያኔ አገዛዝ ፈጽሞት ሊሆን እንደሚችል ለኢሳት የተናገሩት ዶ/ር ኮንቴ፣ የሰጡት ምክንያት በአካባቢው እየተስፋፋ የመጣውን የህዝብ ተቃውሞ ለመጨፍለቅ ሲባል እንዲህ አይነቱን ወንጀል በማቀነባበር በተቃዋሚዎች ላይ መለጠፍ የተለመደ የወያኔ ሴራ ነው ብለዋል።

ወያኔ በኦጋዴን የሚንቀሳቀሰውን የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባር ለመደፍጠጥ የሚያካሂደውን ጦርነት ከአሁን ቀደም በክልሉ በ9 ቻይናውያን እና ከ60 በላይ ኢትዮጵያውያን ላይ ከ4 አመታት በፊት የተፈጸመውን ግድያ ምክንያት በማድረግ እስከዛሬ ድረስ አካባቢውን የጦር ቀጠና ማድረጉ ይታወቃል።

በሰሞኑ ጥቃት 5 የጀርመን፣ የሀንጋሪና አስትሪያ ዜጎች ሲገደሉ፣ ሁለት የጀርመን፣ አንድ የአስትሪያና ሁለት የኢትዮጵያ ታጣቂዎች ደግሞ ተይዘው ተወስደዋል።(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በራሳችን ቋንቋ እንማር በማለት ጥያቄ ያቀረቡ የኦሮሞ ተወላጆች ለእስራትና የተለያዩ በደሎች መጋለጣቸውን የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ ገለጠ

የብሄር ብሄረሰቦችን መብትና እኩልነት አስከብሪያለሁ እያለ የሚመጻደቀው የወያኔ አገዛዝ የኦሮሞ ተወላጆች በራሳችን ቋንቋ እንማር በማለት ጥያቄ በማቅረባቸው ለእስራትና የተለያዩ በደሎች ተጋልጠዋል ሲል የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ *ኢሰመጉ( ሰሞኑን ባወጣው መግለጫ ማስታወቁን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈው ሪፖርት ገለጸ«።

ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ( ኢሰመጉ) በሚለው ስያሜው ይታወቅ የነበረው የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ተቋም በአፋኙ የወያኔ አገዛዝ ጫና ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) እንዲለውጥ መገደዱ የሚታወስ ሲሆን ይህ ተቋም ሰሞኑን ባወጣቸው ሁለት ልዩ መግለጫዎች፤ በሀገሪቱ በተለያዩ ቦታዎች የከፋ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እየተፈጸመ መሆኑን አጋልጧል።

ሰመጉ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተፈፅሟል ያለው በደቡብ ክልል፣ በከፋ ዞን፣ በገዋታ ወረዳና ዙሪያ ከ1950 ዓ.ም ጀምሮ የሚኖሩ ቁጥራቸው ከ50ሺህ በላይ በሚገመቱ የኦሮሞ ተወላጆች ላይ መሆኑን ተያይዞ የደረሰን ዘገባ ያመለከተ ሲሆን ኦሮሞዎቹ፤ በሕገ-መንግስቱ የተሰጣቸው መብት እንዲከበር ጥያቄ በማቅረባቸው ምክንያት፤ ለሕገ-ወጥ እስራት፣ ማስፈራራት፣ የቤት እና ንብረት ቃጠሎ፣ ለሕገ-ወጥ የመኖሪያ ቤት ብርበራ፣ በቀበሌ አመራር ላይ እንዳይሳተፉ የመከልከል እና ሌሎችም የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እንደደረሱባቸው በዝርዝር አጋልጡአል።

የሰመጉን መግለጫ ዋቢ በማድረግ ዘጋቢያችን በላከው ዘገባው፤ በዶማ ቀበሌ ጳጉሜ 2 ቀን 2003 ዓ.ም የ10 ቀበሌ ሕዝብን በመጥራት ስብሰባ በተደረገበት ወቅት፤ የወረዳው ባለስልጣናት በገዋታ ወረዳ የሚኖሩ የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄዎች፡- “ልክ ስላልሆነ አይፈቀድላቸውም፤ በእኛ ስር ዝቅ ብላችሁ መኖር አለባችሁ። ለዚህ ፈቃደኛ ካልሆናች፤ አሸባሪዎች ናችሁ” መባላቸውንም አክሎ ገልጹአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ፍርሃትን ማሸነፍ፤ ወያኔን ማስወገድ ነው!!!

በሕዝብ ውስጥ ፍርሃትን ማንገስ የተለመደ የአምባገነኖች የመጨቆኛ መሣሪያ ነው። ፍርሃት ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ዜጎች ተዋርደው፣ ተረግጠውና ተቀጥቅጠው እንዲገዙ የማድረግ አቅም አለው። ፍርሃት ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ገዢዎች የሌላቸውን ጉልበት ያላቸው ያስመስላል።

ሆኖም ግን ፍርሃት ያቆመው ሥርዓት ለመናድ ጊዜ አይፈጅበትም። ፍርሃት ያቆመው የበርሊን ግንብ በሰዓታት ውስጥ ፈራርሷል። በፍርሃት ሕዝባቸውን አንቀጥቅጠው የገዙ የቱኒዚያው ቤን ዓሊ፣ የግብጹ ሙባረክ እና የሊቢያው ጋዳፊ ፍፃሜያቸው እንዴት እንደነበር ከጥቂት ወራት በፊት ያየነው ነው። ሕዝባቸውን በፍርሃት ቀፍድደው በመግዛት የታወቁት የየመኑ አብዱላ ሳልህና የሶሪያው ባሽር አልአሳድም ሊደረመሱ ተቃርበዋል።

ኢትዮጵያዊያንን በፍርሃት ቀፍድዶ እየተጫወተብን ያለ የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ውድቀትም ተመሳሳይ እንደሚሆን ጥርጥር የለንም።

"ፍርሃትን እንዴት ነው የምናሸንፈው?" ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ማግኘት ወቅታዊና አስፈላጊ ነገር ነው።

በግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍርሃትን ማሸነፊያ መንገዶች ከሌሎች መማር አያስፈልገውም። ፍርሃትን ማሸነፊያ መንገዶች ከራሳችንን ጀግኖች መማር እንችላለን ብሎ ግንቦት 7 ያምናል፤ የሚከተሉትንም ለአብነት ይጠቅሳል።

### አብነት አንድ

የዳውሮው ወጣት መምህር የኔሰው ገብሬ ፍርሃትን እንዴት ሊያሸንፍ ቻለ?

መምህር የኔሰው ገብሬ ከሥራ ተባሯል፤ ታስሯል፤ ተንገላቷል። በደል አንገሽግሾታል። ኅዳር 1 ቀን 2004 ዓ.ም. በእርሱ ላይ እንደደረሰው ሁሉ ያለአግባብ የታሰሩ ወዳጆቹ ወደ ሚቀርቡበት የወረዳው ፍርድ ቤት አመራ። ዳኛው የታዘዙትን ተጨማሪ ቀጠሮ የመስጠት ውሳኔ አስተላለፉ። የየኔሰው ፍርሃት እዚህ ጋ አበቃ። ከፍርድ ቤቱ እንደወጣ ወደ አካባቢው አስተዳደር ቢሮ ሄደ። ባለስልጣኖቹ ስብሰባ ላይ ናቸው። የአስተደደሩ ቢሮ በረንዳ ላይ

> *"በደል በዛ!!! ፍትህ በሌለበት አገር መኖር አልችም!!! በዚህ ሁኔታ መኖር ኑሮ አይባልም!!! ግፍና መከራ እያየሁ መኖር አልችልም!!!"*

እያለ ቤንዚን በራሱ ላይ አርከፍክፎ እሳት ለኮሰ። ኅዳር 4 ቀን 2004 ዓ.ም. ኢትዮጵያም አንድ በፍትህ እጦት የተከፋና የተቆጣ ልጇን አጣች። ለእኛ ግን ትምህርት ሆነ። የየኔሰው ገብሬ ቁጣ በውስጡ የነበረው ፍርሃትን አሸነፈ።

### አብነት ሁለት

አዴት በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን የምትገኝ ከተማ ናት። ጥር 2 ቀን 2004 ዓ. ም. የወረዳው የወያኔ ሹማምንት እንደልማዳቸው "ህገ ወጥ ግንባታ" በሚል ሰበብ የድሆችን ቤት ያፈርሳሉ። እናቶችና ህፃናት አለቀሱ። ነገር ግን የድሆች ዋይታ ለቤት አስፈራሾቹ ሹማምት ጆሮዎች የሚጥሙ ሙዚቃዎች ናቸውና ሥራቸውን አላሰናከላቸውም። የአዴት ከተማ ወጣቶች "መውደቂያ ሳትሰጧቸው የድሆችን ጎጆዎች አታፈርሱ" ሲሉ ተቃወሙ። ሹማምንቱ ግን በፓሊሶች ታጅበው በማንአለብኝነት ቤቶቹን ማስፈረስ ቀጠሉ።

ቤቶቻቸው እየፈረሰባቸው ያሉት ዜጎች እና የከተማው ወጣቶች ከመለማመጥ ወደ መሰዳደብ፤ ትንሽ ቆይቶም ወደ ድንጋይ መወርወር ተሸጋገሩ። ፓሊሶች ለድንጋይ ውርወራ የጥይት ምላሽ ሰጡ። የአንዳንዶቹ ወጣቶች ፍርሃት እዚህ ጋ አበቃ!!!

ከተበዳዮች ጥቂቶቹ የፖሊሶችን ጠመንጃ በዱላ ቀሙ። የድሆች ቤቶች አፍራሽ ግብረኃይልን ሲመሩ የነበሩትን ተኩሰው ገደሉ፤ ሌላኛውን ክፉኛ አቆሰሉ። የቆሰለውም የወያኔ ሹም ጥቂት ቆይቶ ሞተ። የአዴት ወጣቶች የፓሊሶቹን መሳሪያዎች ነጥቀው ተሰወሩ። የበደል መብዛት የአዴት ወጣቶች ፍርሃትን እንዲያሸንፉ አደረጋቸው።

በዳውሮ እና በአዴት የተፈጸሙት ነገሮች በርካታ የጋራ ባህሪያት አላቸው።

ሁለቱም አጋጣሚዎች በደል ሲበዛ እንደሚመር እና የመረረው ሰው እንደማይፈራ ያስገነዝቡናል። በወያኔ ላይ ለመነሳት የምንፈራው በደሉ ገና ዘልቆ ስላልተሰማን ይሆን? ከሆነ አሁን ወያኔ እያደረሰብን ያለውን በደል ጥልቀት ይሰማን፤ ይመመን።

ያመሩሩ ሰዎች ምን ዓይነት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው መመሪያ እንዲሰጣቸው እንደማይጠብቁ በሁለቱም አጋጣሚዎች አይተናል። የዳዉሮው ወጣት፣ መምህር የኔሰው ገብሬ "እኔ ብቻዬን ምን አቅም አለኝ?" አላለም። በራሱ ላይ በወሰደው ቆራጥ እርምጃ ሁላችንንም ሞገተን። እሱም ስሙን ከመቃብር በላይ አኖረ። የአዴት ከተማ ወጣቶችም "የጦር መሣሪያ የለንም፤ የጦር ልምምድ አላደረግንም" ብለን አላማረሩም። ለንብረታቸውና ለመብቶቻቸው ዱላና ድንጋይ ይዘው ተሰለፉ። በዱላና በድንጋይ ጠመንጃ ነጥቀው፤ ባለጠመንጃውን በራሱ ጠመንጃ ገድለው ተሰወሩ።

ይህ ነው ሕዝባዊ አመጽ ማለት። ይህ ነው ሁለገብ ትግል ማለት። ይህ ነው ግንቦት 7 እንዲመጣ የሚታገለው ኢትዮጵያዊ ጀግንነት።

ሁኔታዎች ተስፋ ሰጪ ናቸው። ኢትዮጵያዊያን "የነፃ አውጪ" መምጣትን መጠበቅ እየተው ነው። ግለሰብን ነፃ የሚያወጣው ራሱ ግለሰቡ ነው። ሕዝብን ነፃ የሚያወጣው ራሱ ሕዝቡ ነው። ግለሰብም ሕዝብም ነፃ የሚወጣው በቅድሚያ ፍርሃትን ሲያሸንፍ ነው።

ስለሆነም ወያኔ በዘራብን ፍርሃት ላይ እናምጽ። በፍርሃታችን ላይ ባመጽንባት ቅጽበት ወያኔ የለም። ያለእኛ ፍርሃት ወያኔ የጠዋት ጤዛ ነው፤ አሊያም ጉም ነው። ያለ እኛ ፍርሃት ወያኔ ትቢያ ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!!**

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በሽብርተኝነት ወሂኒ ያወረዳቸው ጋዜጠኞችና ተቃዋሚ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ዘመን የህግ የበላይነትና የፍርድ ቤቶች ገለልተኝነት በአገሪቱ ውስጥ ጨርሶ እንደሌለ በተደጋጋሚ ሲገልጽ የኖረው አለም አቀፉ ሂውማን ራይትስ ወች የወያኔ ፍርድ ቤት የሰጠውን ይህንን ብይን ወዲያውኑ ውድቅ አድርጓል። ህውማን ራይትስ ዎች ዛሬ ባወጣው መግለጫ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሆን ብሎ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽን ህገመንግሥታዊ መብት የሚጻረር በመሆኑ፣ አገዛዙ ጉዳዩን በአፋጣኝ ውድቅ አድርጎ ጋዜጠኞችን እንዲፈታና በእስር ቤት እያሉ የደረሰባቸውን አሰቃቂ ድብደባ የሚያጣራ ቡድን በአስቸኳይ እንዲያቋቁም ጠይቋል።

የድርጅቱ የአፍሪካ ተማራማሪ የሆኑት ላታሺያ ባድር ለኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ኢሳት በሰጡት ቃለመጠይቅ እንደገለጡት የኢትዮጵያ የጸረ ሽብርተኝነት ህግ ገለልተኛ ዘገባን እና ሰላማዊ ተቃውሞን ለማፈን ተብሎ የተደነገገ በመሆኑ ህጉ ሊቀየር ይገባዋል ማለታቸው ተዘግቦአል።

ሂውማን ራይትስ ዎች የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በተለያየ የአገራችን ክፍሎች በዜጎች ላይ የሚፈጽማቸውን ሰቆቃዎች እየተከታተለ በማጋለጡ ምክንያት የወያኔ ቁንጮዎች ድርጅቱን ሲያሻቸው ከተቃዋሚዎች ጋር የወገነ ካልፈለጉ ደግሞ የምዕራባዊያን ርዕዮተ አለም በኛ ላይ ለመጫን የሚንቀሳቀስ እያሉ ይከሱታል።

መለስ ዜናዊ የሥልጣን እድሜውን ለማሳጠር በሚንቀሳቀሱት ዜጎች ላይ የማያዳግም እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችለው አርቅቆ በሥራ ላይ እንዲውል ባወጣው የሽብርተኝነት አዋጅ በሽብርተኝነት የተከሰሰ ሰው አነስተኛ ቅጣት የ15 አመት እስራት ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ የሞት ነው።

በተያያዘ ዜና ህጋዊ ፓርቲን ሽፋን በማድረግ በሽብርተኝነት ለተፈረጀው ኦነግ ይሰራሉ በሚል በነ አቶ በቀለ ገርባ የክስ መዝገብ የተከሰሱት የኦፌዴን ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበር አቶ በቀለ ገርባ፣ የኦህኮ ፓርቲ ኃላፊ አቶ ኦልባና ለሊሳ እና ሌሎች ሰባት ተከሳሾች ላይ የወያኔ ዐቃቤ- ህግ 4 ቀሪ ምሥክሮቹን ትናንት ረቡዕ ማቅረቡ ተዘገበ፡፡

ተከሳሾች ለወያኔው የፖለቲካ ፍርድ ቤት እንደተናገሩት ዐቃቤ-ህግ የተባለው የካድሬዎች ስብስብ በገንዘብ፣ በጥቅማ- ጥቅም የተገዙ ቁጥራቸው 22 የሆኑ የደህንነትና የወያኔ ተለጣፊ ድርጅት አባላትን ምሥክር አድርጎ አቅርቦባቸዋል።

አንድ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአስተዳደር ሠራተኛ ለኢሳት ሪፖርተር እንደገለጹት፤ መንግሥት ለኦነግ አደረጃጀት ቅርበት አላቸው ያላቸውን 25 ግለሰቦች በተለያየ ጥቅማ- ጥቅም ደልሎ እና ደብል ኤጀንት ወይም በሁለት ቢላዋ የሚበሉ የደህንነት ሠራተኞቹን ከሞያሌ፣ ባሌ፣ አርሲ ነገሌ፣ አምቦ እና ነቀምት በማሰባሰብ ናዝሬት አንድ ሆቴል ውስጥ አስቀምጦ የአቃቤ- ህግ ምስክርነት አሰጣጥ ሲያለማምዳቸው ከቆየ ቡኋላ ከ25ቱ በጥሩ ሁኔታ ሊመሰክሩ ይችላሉ የተባሉ 22 ሰዎችን መልምሎ ለምስክርነቱ አቅርቦአል።

እንደዜና ምንጮቻችን ዘገባ ከተከሳሾቹ አንዱ "እኔን በቁጥጥር ሥር ያዋለኝ የደህንነት ሠራተኛ ሚስቴን አግብቶ በቤቴ ውስጥ በመኖር ላይ ይገኛል፣ በምስክርነት የመጡብን ሰዎች በጥቅማ- ጥቅም የተገዙ የኦህዴድ አባላትና የደህንነት ኃይሎች ናቸው የሚል ወረቀት ጽፎ በድብቅ ለታዳሚዎች " አሰነብቧል፡፡

በታሳሪዎቹ ላይ መለስ ዜናዊና ጥቂት ግብረአበሮቹ አስቀድመው ያስተላለፉትን ቅጣት ለመስጠት ድራማውን እያጧጧፉ ያሉት ታዛዥ የፍርድ ቤቱ ዳኞች የቀረቡትን የዐቃቤ-ህግ ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃዎች አይቶ ለይስሙላ ያህል ተከሳሾች ክሱን ይከላከሉ ወይስ አይከላከሉ የሚለውን ብይን ለመስጠት ለጥር 29 ቀን 2004 ዓ.ም ተለዋጭ ጊዜ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

## እናንተ ዓይን ያያችሁ እዩ !!! ጆሮም ያላችሁ ስሙ!!!

ከሰሞኑ ስለ ንቅናቄያችን የሚሰጡ አስተያየቶች በርክተዋል። አንዳንዶቹ ከጳጳሱ በላይ ካቶሊክ ሁነው ስለ ድርጅታችን ሁኔታ ከጣሪያ በላይ እየጮሁ የሚያደምጣቸውን ፍለጋ ሲኳትኑ ሰንብተዋል፡፡ ጠልሰምም ጠልሰመዋል። ስለድርጅታችን ይሄ ነው የሚባል እውቀት ሳይኖራቸው የማያውቁትን ሲለፈልፉ ጥራዝ ነጠቅነታቸውንም ገልጠው አሳይተውናል። እንዲህ በየአደባባዩ የሚያደምጣቸውን ፍለጋ ለሚጮሁ ዓይናችሁን ክፈቱና ተመልከቱ ጆሮአችሁንም አንቁና አድምጡ ከማለት በቀር የምንለው ሌላ ነገር የለንም።

ስለንቅናቄያችን ግንዛቤ ሳይኖራችሁ ከጣሪያ በላይ የምትጮሁ ሆይ ስሙ እኛ ማን እንደሆንን ደግመን ደጋግመን እንነግራችኋለን። ግንቦት ሰባት የፍትህ፤የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ኢትዮጵያዊ ድርጅት ነው። ግንቦት ሰባት የብዙ የአገሪቷ ወንዶችና ሴቶች ልጆች የፈጠሩት ንቅናቄ ነው።ግንቦት ሰባት ውስጥ የተሰባሰቡ ኢትዮጵያዊያን ከጎሳ ወገንተኝንት ተላቀው እጅግ ከፍ ላሉ ምክንያቶች ማለትም ለፍትህ፤ ለነጻነት እና ለእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ወግነው የቆሙ ዜጎች የተሰባሰቡበት ንቅናቄ ነው። የንቅናቄውም ህልም በአገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ፍትህ ነግሶ፤ ነጻነት ሰፍኖና እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተገንብቶና ዜጎቿ በእኩልነት የሚኖሩባት አገር ተሥርታ ማየት ነው።

እኛ ኢትዮጵያዊያን በመሆናችን ኢትዮጵያዊ ከሆነ ኃይል ጋር ተባብሮና ተከባብሮ በአንድነት መሥራት አገራችንን ከዘረኞችና ከዘራፊዎች ለመታደገ አማራጭ የሌለው መንገድ መሆኑንም በጽኑ እናምንበታለን። ይህንንም እውን ለማድረግ ኢትዮጵያ የተባለች አገር መኖሯን ከሚቀበልና የመለስ ዜናዊን ዘረኛና ዘራፊ አገዛዝ ለማወገድ ከሚሰራ ከማንኛውም ኃይል ጋር እንተባበራለን።አብረንም እንሰራለን።ይህንን እንዳናደርግ ሊያቆመን የሚችል ኃይል የለም።የምናምንበትን ለመሥራት የሚያስኬዱ መንገዶችን ሁሉ እንሄዳለን።ለዚህ የማንንም ቡራኬ የምንፈልግ አይደለንም።

ግንቦት ሰባት የሚሠራውን ሥራ ድምጻቸውን ከጣሪያ በላይ ከፍ አድርገው ለሚጮሁ ሁሉ እያሳየ ቡራኬ የሚፈልግ ድርጅት አይደለም። ንቅናቄው ያከናወናቸውን ተግባራት እኔ አደረኩት ብሎ ለፕሮፖጋዳ ፍጆታ የማዋል ፍልጎት ያለው ድርጅትም አይደለም። ስለ ንቅናቄያችን ሌሎች የሚናገሩለት ከበቂ በላይ ነው። ድርጅታችን የሚያደርገውን ያዋጣኛል ብሎ በሚያምንበት መንገድ ሁሉ ያደርገዋል እንጂ ቁጭ ብለው የሚተቹትን ስሜት እያዳመጠ ለዚያ ስሜት ማርኪያ የሚያደርገው አንዳች ነገር የለም። ግንቦት ሰባት የሚያደርገውን ለራሱና ለቆመለት ዓላማ ብሎ ያደርገዋል እንጂ ማንንም ለማስደሰት ብሎ አያደርግም። ይህ ሊታወቅ የሚገባ እውነት ነው።

መለስ ዜናዊና ጀሌዎቹ የታሪክ እስረኞች አድርገው ሊያኖሩን ለረዥም ግዜ ሳይታክቱ ሠርተዋል። ልዩነቶቻችንንም ፈትለውና አድርተው በልዩነቶቻችን ጠልፈው ጥለውን ከወደቅንበትም እንዳንነሳ ሊያደርጉን ሌት ተቀን እየሰሩ ነው።ወደ ፊት ሳይሆን ብዙ ዘመን ወደ ኋላ ሂደን የዚያ ዘመን ታሪክ እስረኛ እንድንሆን ሊያደርጉን የሚችሉትን ሁሉ እያደረጉ ነው። ግንቦት ሰባት ብዙ ዘመን ወደ ኋላ ሂዶ ሙታንን ቀስቅሶ ከሙታን ጋር ውጊያ የሚገጥም ድርጅት አይደለም። ግንቦት ሰባት ካለፈው ስህትተ ተምሮ ወደ ፊት የሰው ልጆች መብት የተከበረባት አገርን ለመፍጠር ይሰራል እንጂ ራሱን የታሪክ እስረኛ አድርጎ ከሙታን ጋር ሙግት የሚገጥም ድርጅት አይደለም።

ዛሬም ወደ ፊትም ደግመን ደጋግመን የምንናገረው ከታሪክ እስረኝነት ራሱን ነጻ ያላወጣ ሌላውን ነጻ ሊያወጣ ብቃት ይኖረዋል ለማለት የምንቸገር መሆናችንን ነው። ከሙታን ጋር ሙግት የገጠመ ቡድን ህያው ጠላቱን ለመዋጋትና ነጻነቱን ለመቀዳጀት አቅም ኑሮት ለዜጎች ነጻነት ይቆማል ለማለት አይቻልም። የትላንቱን ቁስል መልሶ መልሶ ማውራት ነገ አብሮ የተሻለ ቁም ነገር ለመሥራት የሚችልበትን ግዜና ጉልበትን ያባካናል እንጂ ለዜጎች የሚፈይደው ምንም በጎ ነገር የለውም። ትናንትና ከነስህተቱና ከነመጥፎ ተግባሩ ላይመለስ አልፏል።ያን ስህተት ዛሬ ካልደገምኩ ሙቼ እገኛለሁ ማለት ከሞኝነት በላይ ነው።ትላንት በብዙ ዜጎች ደምና አጥንት ላይ የተገነባን አገር ዛሬ ካልበተንኩ አልመለስም ማለት ቅዥት ነው። ግንቦት ሰባት የዚህ ዓይነት ሞኝነትም ሆነ ቅዥት የለውም። ግንቦት ሰባት ከትላንቱ ስህተት ትምህርት ወስዶ ነገ በኢትዮጵያችን የተሻለ ሁኔታ ለመፍጠር የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነው። ግንቦት ሰባት በኢትዮጵያ ውስጥ ትላንት በወገኖቻችን ላይ የደረሰው በደል ዛሬም ወደፊትም እንዳይደገም በርትቶ የሚሰራ ድርጅት እንጂ ሙታንን እየወቀሰ ግዜውን በከንቱ የሚያባክን ድርጅት አይደለም።

በታሪክ እስርኝነት ተጽእኖ ሥር ያለ የትላንቱን ቁስል እያሰበ ከበቀልና ከጥላቻ የዘለለ በጎ ነገር ማድረግ ይችላል ለማለት አንችልም። የበቀለኝነት ስሜት አገር ያፈርሳል እንጂ አገር አይገነባም። በዚያ ስሜት መኖር የመለስ ዜናዊ ስሜት ህግ እንደሆነ እንዲቀጥል ያደርገዋል እንጂ መለስና ጀሌዎቹ ከህግ በታች እንዲሆኑ አያደርግም። በትላንቱ ታሪክ ታስሮና በበቀል ስሜት ተወጥሮ መኖር ፍትህን ያጠፋል እንጂ ፍትህን አያመጣም። በትላንትናው ታሪክ ታስሮና በበቀል ስሜት ተወጥሮ መኖር እውነትን መነጋገር የምንችልበትን መድረክ ያጠባል እንጂ መድረኩን አያሰፋም። አብሮነትን ያላላል እንጂ አያጠብቅም።

በድርጅታችን የተሰባሰቡ ኃይሎች ከታሪክ እስረኝነት ተፈተው የትላንቱን ሳይሆን የመጪው ትውልድ እጣ ፈንታ ብቻ የሚያሳስባቸው ናቸው። ግንቦት ሰባት የሚመጣው ትውልድ ተደላድሎ በሠላምና በደስታ ሊኖር የሚችልባት አገር እንድትፈጠር ቀንና ማታ የሚሰራ ድርጅት እንጂ ያለፈው ትውልድ የሠራው ችግር ላይ አተኩሮ አተካሮ ፈጥሮ እርባና ቢስ በሆን ንትርክ ግዜውን የሚያጠፋ ድርጅት አይደለም። እኛን ይበልጥ የሚያሳስበን የነገው እንጂ የትላንቱ አይደለም። ለነገው እንሰራልን እንጂ በትላንቱ ላይ ስንነታርክ ግዜያችንን አናጠፋም።

በመጨረሻም ወገንተኝነታችን ከፍትህ፤ከነጻነት እና ከዴሞክራሲ ጋር እንጂ ከማንኛውም ጎሳ ጋር እንዳይደለ ድምጻችንን ከፍ አድርገን እንነግራችኋለን። በአገራችን ሁሉም ዜጋ እኩል ሁኖ የሚኖርበት ሁኔታ እንዲፈጠር እንጂ አንዱን ጎሳ አንግሰን ሌላውን ጎሳ ተገዢ ለማድረግ የምንሰራ አለምሆናችንን ደግመን እንነግራችኋለን። ዜጎች በገዛ አገራቸው ፖለቲካ ውስጥ ወሳኝ የሚሆኑበትን ሁኔታ ለመፍጠር እንሰራለን እንጂ እኛ እናውቅልሃለን የምንል አይደለንም። ከጣሪያ በላይ ጮኻችሁ ስለ ንቅናቄያችን የምትለፈልፉ ጆሮአችሁን ክፈቱና ይህን የምንነግራችሁን እውነት ስሙ። ጨርሰናል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ !!**

## የጋምቤላ ክልል ፕሬዳንት ሰሞኑን የሰጠው ምስክርነት በ1996 ዓም አኝዋኮች ላይ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

አገዛዙ የሰፈራ ፕሮግራሙ አላማ መሬት ለኢንቨስተሮች ለመስጠት ሳይሆን ነዋሪዎች የተሻለ ምቾች የሚያገኙበትን ሁኔታ ለመፈልግ ነው በማለት የሚያቀርበውን ማስተባበያ ሚስተር ኢግላንድ እንደማይቀበሉትም አሳዉቀዋል። በተጨማሪም ይህን በህዝብ ላይ የሚደርሰውን ስቃይ የውጭ አገር ለጋሽ አገሮች በተዘዋዋሪ መንገድ እንደሚያበረታቱ ሚ/ር ጃን ኢንግላንድ ገልጠዋል።

የሂውማን ራይትስ ወች ተመራማሪ የሆኑትን ቤን ራውለንስን የክልሉ ፕሬዚዳንት የሆኑዉ ኦሞድ ኦባንግ በ1994 እና 95 ዓም በአኝዋክ ህዝብ ላይ በደረሰው ጭፍጨፋ እጁ እንዳለበት ማመኑ ለበለጠ ምርመራ በር ይከፍታል ማለታቸው በዘር ፍጅት ወንጀል ክስ እየቀረበበት ያለውን መለስ ዜናዊንና ጥቂት ግብረአበሮቹን የበለጠ እረፍት የሚነሳ አስደንጋጭ ዜና እንደሆነ ይገመታል።

ኦሞድ ኦባንግ በቅርቡ በአኝዋኮች ላይ በደረሰው ጭፍጨፋ የምጠየቅ ከሆነ፣ ትእዛዙን የሰጠኝ መለስ ዜናዊም መጠየቅ አለበት በማለት በመናገሩ የፓርቲ ሊቀመንበርነት ቦታውን እንዲያጣ፣ በሂደትም ከፕሬዚዳንትነት ስልጣኑ እንዲነሳ ለያደርገዉ እንደሚችል የጋምቤላ ምንጫጬ መናገራቸው መዘገቡ ይታወሳል።
በጋምቤላ ከ9 አመት በፊት የጸጥታ ሀይሎች ባደረሱት ጭፍጫፋ ከ500 በላይ ሰዎች መገደላቸው ይታወሳል። የመለስ ፓርቲ ጉዳዩን እራሱ በአቋቋዉ አጣሪ ኮሚቴ አስመርምሮ፣ የመከላከያ ሰራዊቱ ጥፋት አልፈጸመም ማለቱም ይታወሳል።

ይሁን እንጅ በርካታ ኢትዮጵያውያን እና እንደ ጄኖሳይድ ወች የመሳሰሉት ድርጅቶች የመለስ መንግስት በአለማቀፉ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ በመወትወት ላይ ናቸው።

ይህ በዚህ እንዳለ የጋምቤላ ፕሬዝዳንት ኦማት ኦባንግ ሙስናን ለማጣራት ከወያኔ ፌዴራል ቢሮ በተላኩት ሰዎች ፊት በ2003ቱ የአኝዋኮች ጭፍጨፋ የሚገደሉትን ሰዎች ስም ዝርዝር አዘጋጅ ተብሎ መታዘዙንና በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መፈጸሙን ፤ ይህ በሃላፊነት የሚያስጠይቅ ከሆነ ግን መሳሪያና ወታደር በመላክ ጭፍጨፋውን የፈጸመው መለስ ዜናዊም መጠየቅ እንዳለበት መናገሩን በመቅረጸ ድምጽ በድብቅ ተቀርጾ የወጣ ማስረጃ እንዳረጋገጠ የዘገበው ቪ.ኦ.ኤ. የመለስ ዜናዊ ቀኝ እጅ የሆነው በረከት ስሞኦን ይህንን ውንጀላ እንዳስተባበልም ገልጾአል።

በረከት ስሞኦንና ሽመልስ ከማል በአገራችን የተለያዩ ግዛቶች የሚፈጸሙትን ተመሳሳይ ሰቆቃዎች ፤ እስርና ግድያን አይኔን ግንባር ያድርገው በማለት እንደሚኪዱ ከአገር አልፎ በውጪው አለምም ይታወቃል። ላለፉት 20 አመታት በረከት ስምኦን በየአደባባዩ ከሰጣቸው መግለጫዎች ተአማንነትን ያገኘው ሼህ አላሙዲን ታመምኩ ባለ ቁጥር አንጠልጥለው ለህክምና ወደውጪ እንደሚልኩት አለመካዱና ወግ እንዳይቀርበት አሳተምኩት ላለው ድርቶ መጽሃፍ ከኙሁ ሰው ገንዘብ መቀበሉን በአደባባይ መግለጹ ብቻ እንደሆነ በቅርበት የሚያውቁት ይናገራሉ።

በጋምቤላ ክልል ሙስናን ለማጣራት ተብሎ ከወያኔ ፈደራል ቢሮ ተልኮ የነበረው ቡድን በክልሉ ከተሰማሩት ባለህብቶች የተዋጣ ከሶስት ሚሊዮን ብር በላይ መደለያ በመቀበል የደረሰበትን የምርመራ ውጤት አድበስብሶ እንደተመለሰ ለማወቅ ተችሎአል።

በመሬት ቅርምትና በኮንስትራክሽን ሥራ በክልሉ የተሰማሩት ሃብታሞች የወቅቱ የክልሉ ፕሬዝዳንት ኦማት ኦባንግ ከሃላፊነቱ ቢነሳ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ሼህ አላሙዲን ስፖርተኞችን በገንዘብ በመደለል አፍቃሪ ወያኔ የሆነ እግር ኳስ ፌዴሬሽን በሰሜን አሜሪካ ለማቋቋም ወደግማሽ ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ መመደባቸው ታወቀ።

## ስፖርተኞቹ "በደም የተነከረ ገንዘብ አንፈልግም!" ሲሉ ተቃወሙ

ወያኔ ወደስልጣን ከመምጣቱ በፊት የተቋቋመውና በየአመቱ ለበርካታ ኢትዮጵያዊያን መሰብሰቢያ በመሆን 28ኛ አመቱን ሊያከብር ወራቶች ብቻ የቀሩት የሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያዊያን ስፖርት ፌዴሬሽን፤ በሼህ አላሙዲን የገንዘብ ስጦታ ምክንያት መተራመስ ከጀመረበት ቅርብ አመታት ወዲህ በገንዘብ ተደልለው ፌዴሬሽኑን በወያኔ ጉያ ውስጥ ለማስገባት በሚያሴሩት ጥቂት አባላቱና ሴራውን ለማክሸፍ በሚታገሉ ብዙሃን መካከል የተቀሰቀሰው ትንቅንቅ አለማብቃቱን የሚያመለክቱ ማስረጃዎች ከስሞኑ ብቅ ብቅ ማለት መጀመራቸውን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከዋሽንግተን ዲሲ ገለጠ።

ባለፈው አመት አትላንታ ላይ ተደረጎ በነበረው አመታዊ የስፖርት በዓል ላይ በክብር እንግድነት እንዲገኙ በብዙሃን ድምጽ ተጋብዘው የነበሩትን የቀድሞ የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር የዳኛ ብርቱኳን ሚደቅሳን ግብዣ ለማሰረዝ ሞክረው ያልተሳካላቸው የፌዴሬሺኑ አመራር አባላት ከብዙሃኑ ጋር በገጠሙት አታካራ ምክንያት ተነስቶ የነበረውን ውዝግብ በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ እንደነበር የገለፀዉ ዘጋቢያችን በምርጫው የተሸነፉት ጥቂት ሰዎች ከሼህ አላሙዲን ጋር በመመሳጠር ብዙ መቶ ሹህ ዶላር ገንዘብ ከተቀበሉ ቦኋላ ሌላ ተለጣፊ ፌዴሬሽን ለማቋቋም ጥረት መጀመራቸው የአደባባይ ምስጥር ሆኖአል ብሎአል።

በስፖርት በአል ሥም በየአመቱ የሚሰባሰበው ኢትዮጵያዊ አጋጣሚውን ተጠቅሞ ስለአገሩ ጉዳይ እንዳያነሳ ክፍፍል ለመፍጠር ታጥቆ የተነሳው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፤ የአገሪቱን ሃብት ጠቅልሎ በእጁ ያስገባለትን ሃብታሙን ሼክ በመጠቀም በርካታ ገንዘብ በማፍሰስ በየስቴቱ ያሉትን ክለቦች ዳጎስ ባለ ገንዘብ በመግዛት የፊታችን ጁላይ ወር ዋሽንግተን ዲሲ ላይ የመጀመሪያውን ዉድድር ለማዘጋጀት በ60ሺ ዶላር ወጪ ስታዲዬም እንደተከራየ ለማወቅ ተችሎአል።

ከራሳቸው የግል ጥቅም አርቀው በአገርና በወገን ላይ የሚፈጸመውን በደል ለማየት የተሳናቸውን ሰዎች በገንዘብ ሃይል በመግዛት ከአገሩ ተሰዶ የሚኖረው ህብረተሰብ በጋራ የሚገናኝበትን መድረክ ለማጥበብ እየተንቀሳቀሰ ያለውን ይህንን የወያኔ ስውርና ግልጽ ወንጀል ለማክሸፍ በሰሜን አሜሪካ የተለያዩ ክፈለግዛቶች የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በየአካባቢያቸው እንቅስቃሴ መጀመራቸው ታውቆአል።

በሼህ አላሙዲን ገንዘብ ተመደቦለት ሌላ ፌዴሬሽን ለማቋቋም እየተንቀሳቀሰ ያለው ቡድን ለያንዳንዱ ስፖርተኛ የሆቴልና የአየር ትራንስፖርት ወጪ ለመሸፈን ቃል ተገብቶ ተጠርቶ በነበረው ስብሰባ ላይ እንዲገኙ የተፈለጉት ስፖርተኞች "በደም የተጨማለቀ ገንዘብ በግጻ በረከትነት አንቀበልም" በማለታቸው ስብሰባው ሳይሳካ እንዳቀረ የኢትዮጵያዊያን አሜሪካን ለፍትህና ለዲሞክራሲ በሎሳንጀሌስ በሚል ስያሜ የተቋቋመ ማህበረሰብ ባወጣው መግለጫ አስታውቆአል።

በሰሜን አሜሪካ የሚኖሩ አገር ወዳድ ስፖርተኞችና የስፖርት አፍቃሪዎች ይህንን የወያኔ ሴራ ለማክሸፍ በጋራ ለመንቀሳቀስ መወሰናቸውን ከየአካባቢው ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

## በራሳችን ቋንቋ እንማር በማለት ጥያቄ ያቀረቡ የኦሮሞ

. . (ከገፅ 1 የዞረ)

ሰመጉ በመግለጫው ጥያቄ ካቀረቡት የኦሮሞ ተወላጆች መካከል ዕድሜአቸው ከ32 እስከ 62 የሚደርሱ 20 ሰዎች መታሰራቸውን እንዲሁም 32 የሚሆኑ ሰዎች ንብረታቸው እንደተቃጠለባቸውና ከቀያቸው እንደተፈናቀሉ በዝርዝር ማቅረቡንም ሪፖርተራችን ገልጹአል።

ሰመጉ አያይዞ ባወጣው መግለጫ ላይ እንዳመለከተው ስፋቱ 20 ጋሻ መሬት ላይ 60 ሔክታር የተፈጥሮ ፣ 15 ሔክታር የሚሊኒየም ፓርክ እና በባለ ተፋሰስ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ሕዝቡ የተከለው 30 ሔክታር የሚገመት ባህርዛፍና ሌሎች ዛፎችን የላንቱ ቀበሌ የመሬት ዴስክ ኃላፊና የቀበሌው ሊቀመንበር፤ ከአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ የካቢኔ አባላት፤ እንዲሁም ከዞንና ከክልል ሀላፊዎች ጋር በመመሳጠር በርካታ ባለስልጣናት በሕገ-ወጥ መንገድ መሬት ለራሳቸው፣ ለዘመዶቻቸው፣ መሬት ላላቸው ገበሬዎች፣ ለፖሊሶች፣ ለመንግስት ሰራተኞችና ከሌላ ቀበሌ ለመጡ ሰዎች ያለመመሪያና ደንብ መደልደላቸውን ጠቅሶ ይህን የተቃወሙ 33 ሰዎች ከመስከረም 30 ቀን 2004 እስከ ጥቅምት 16 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ በሕገ-ወጥ መንገድ መታሰራቸውንም ገልጿል።

ምእራባዊያንን በማደናገር አቻ ያልተገኘለት አጭበርባሪው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያዊያን ላይ እየፈጸመ ያለው ግፍና በደል ከመቼውም ጊዜ ወደከፋ ደረጃ ላይ መድረሱን በርካታ የዜና አውታሮችና የመረጃ ድረገጾች በተደጋጋሚ እየገለጹ ያሉት እውነታ ሲሆን፣ አፋኙ የወያኔ አገዛዝ አሁንም ከኔ በላይ ላሳር፣ የብሄር ብሄረሰቦች መብት በኢትዮጵያ እንዳሁኑ ተከብሮ አያውቅም በማለት እንደሚመጻደቅ ይታወቃል።

## በአፋር ብሄራዊ ክልል በተገደሉት 5 የውጪ አገር ዜጎች . .

(ከገፅ 1 የዞረ)

በረከት ስምኦን በተለመደ ውንጀላው ድርጊቱን የፈጸሙት በኤርትራ የሚደገፉ የአፋር አማጽያን ናቸው ብሏል።

የኤርትራ መንግስት የአፍሪካ ህብረት ተወካይ የሆኑት አምባሳደር ግርማ አስመሮም የወያኔን መግለጫ የፈጠራ ክስ በማለት አስተባብለዋል። አምባሳደሩ "ኢትዮጵያ የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ በተቃረበ ቁጥር እንዲህ አይነት ስሜት የሚነኩ ዘገባዎችን በማቅረብ ባህሪ አድርጋዋለች " ሲሉ ተችተዋል።

የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ በመጪው ሳምንት በአዲስ አበባ ይካሄዳል። ከሁለት አመት በፊት በነበረው የአፍሪካ ህብረት ጉባኤ ሳምንት ኢትዮጵያ ኤርትራ አዲስ አበባን ባግዳድ ለማድረግ አቅዳለች በማለት ክስ አሰምቶ ነበር።

አሁንም ተመሳሳይ ክስ በወያኔ በኩል መቅረቡና ችግሮች ሁሉ ተከስቱ የሚባለው የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ሲቃረብ መሆኑ ሆን ተብሎ የተደረገ ይሁን በድንገት የቀረበ የታወቀ ነገር የለም።

ዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በአገሪቱ ሰላም ሰፍኗል እያለ ዘወትር ቢናገርም፣ በአፋር እና በኦጋዴን እንዲሁም በሰሜን ኢትዮጵያ ጠረፋማ ቦታዎች በነጻነት መንቀሳቀስ አይቻልም። ይህ በእንዲህ እንዳለ የውጭ አገር ቱሪስቶችን ግድያ አስመልክቶ ኢትዮጵያውያን የተለያዩ አስተያየቶችን በድረገጾች እየሰጡ ነው።

የገዢው ፓርቲ ደጋፊዎች ከኤርትራ ጋር ጦርነት እንዲካሄድ ሲወተውቱ፣ ሌሎች ደግሞ ይህን የፈጸመው እራሱ ወያኔ ነው ይላሉ። ወያኔ በቅርቡ "አኬልዳማ" የሚል ድራማ መስራቱ እና በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ማጣቱ አሁንም የሽብር ጥቃት አደጋ መኖሩን ለማሳየት ብሎ የፈጸመው ሊሆን እንደሚችል አስተያየቶች ቀርበዋል።

በተያያዘ ዜና ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በሽብር ፈጣሪው የኤርትራ መንግስት ላይ የማያዳግም ርምጃ ካልወሰደ የኢትዮጵያ መንግስት አስመራ ውስጥ ያለውን መንግስት የመከላከል ሕጋዊ ርምጃ ለመውሰድ ይገደዳል ሲል የመለስ መንግስት ማስታወቁ ተዘገበ። የወያኔ ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ማበወጣው መግለጫ የኢትዮጵያ መንግስት በአሁኑ ጊዜ የኤርትራ መንግስት የሚያካሂዳቸውን የሽብር ድርጊቶችና ለአሸባሪዎች የሚሰጠውን እርዳታ መታገስ የማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል ብሏል፡፡

የሽብር ጥቃቱ ከአንድ ዓመት በፊት በአዲስ አበባ የተካሄደውን የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤ ለማጨናገፍ ታቅዶ የነበረውን የሽብር ሴራ የሚያስታውስ መሆኑን የጠቀሰው የወያኔ መግለጫ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በኤርትራመንግስት ላይ የማያዳግም ርምጃ ካልወሰደ የኢትዮጵያ መንግስት አስመራ ውስጥ ያለውን መንግስት የመከላከል ሕጋዊ ርምጃ ለመውሰድ ይገደዳል ሲል ዝቷል።

የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በውስጥ ቅራኔ ሲወጠርና ህዝባዊ ተቃውሞ ባሰደነገጠው ቁጥር ብሄራዊ ስሜት በማነሳሳት የትኩረት አቅጣጫ ያስለወጠ እየመሰለው የቀድሞ ፈጣሪውና ለሥልጣን ባበቃው ባለውለታው ሻቢያ ላይ ጣቱን መቀሰር የተለመደ ነው የሚሉ በርካቶች ናቸው። አንድ ተቀማጭነታቸው በአዲስ አበባ የሆነ ዲፕሎማት ድርጊቱ ምናልባትም የኢትዮጵያ መንግስት የአለማቀፉ ማህበረሰብ በኤርትራ ላይ ተጨማሪ ጫና እንዲያሳድር በማሰብ ራሱ ቱሪስቶችን ገድሎአቸው ሊሆን እንደሚችል ተናግረዋል።

ዲፕሎማቱ የጥቃቱ ዜና እንደተሰማ የኢትዮጵያን መንግስት ምን ያክል ቱሪስቶች እንደተገደሉና ዜግነታቸው ከየት እንደሆነ ስንጠይቀው መረጃ የለኝም ብሎን ነበር፣ ነገር ግን ጥቃቱን የፈጸመው የኤርትራ መንግስት ያስታጠቃቸው አማጽያን ናቸው በማለት ነግሮናል። የሰዎችን ማንነት ማወቅ የተሳነው መንግስት በምን ያክል ፍጥነት በድርጊቱ የኤርትራ እጅ አለበት እንዳለ ለማወቅ አይቻልም ሲሉ በተዘዋዋሪ መንገድ የኢትዮጵያ እጅ ሊኖርበት እንደሚችል ጠቁመዋል። ኤርትራ ከኢትዮጵያ በኩል ለሚሰነዘረው የጦርነት ዛቻ አንድም ቀን መልስ ሰጥታ አታውቅም። የኢትዮጵያ መንግስትም ኤርትራን እንደሚወጋ ከመዛት ተቆጥቦ አያውቅም።

## የጋምቤላ ክልል ፕሬዳንት ሰሞኑን የሰጠው ምስክርነት . .

(ከገፅ 3 የዞረ)

ያለአግባብ በሙስና በእጃቸው ያስገቡት ቦታና ያለጫረታ የወሰዱት የኮንስትራክሽን ሥራዎች ይጨናግፍብናል የሚል ስጋት ስላደረባቸው ሰውዮቻቸውን ለመከላከል ገንዘብ ከኪሳቸው በማዋጣት ለአጣሪነት ለተላኩት ዘመዶ ዘመድኩንና አለባቸው ንጉሴ መስጠታቸው ታውቆአል።

ይህንን እጅ መንሻ ገንዘብ ያሰባሰቡት ደግሞ አቶ ሸዋየ ብሩ የንግዱ ማኅበረሰብ ሰብሳቢ፣ አቶ ሰይድ ነጋሽ በክልሉ በኮንስትራክሽን ስራ የተሰማሩና የአቶ ኦሞት አባንግ ታማኝ ወዳጅ፣ አቶ ታደሠ ኃይለሥላሴ የአቶ ኦሞት አባንግ የደኅንነት ኃላፊና በኦፕዋክ ንጹሃን ዜጎች ላይ የጅምላ ጭፍጨፋ ሲካሄድ ዋና ተዋናይ እንደነበረ የሚመሰከርበትና በወቅቱ የጋምቤላ ፖሊስ አዛዥ የነበረ፣ ያሲን በላይ የክልሉ መስተዳድር ጽህፈት ቤት ባለሙያ፣ ደሳለኝ ብሩ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ተወካይ፣ መስፍን ዝዋሽኝ የክልሉ የአስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊ፣ ሲሳይ ተስፋዬ ከፋክት ኢትዮጵያ ሎጂስቲክስና የኦሞት የቅርብ ወዳጅ እንደሆኑ ተያይዞ የደረሰን ዜና ያመለክታል። ከፌደራል ቢሮ ለፕሬዝዳንቱ በአማካሪነት የተመደበው የህወሃት ተወካይ አስተባባሪና ጉቦውን አቀባባይ በመሆን ተሳትፎአል ተብሎአል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>፡- በ 358 MB, በ 837 kHz

<u>አጭር ሞገድ</u>፡- በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org